# ብሔራዊ አገልግሎት

በዓመቱ መጀመሪያ ላይ ጥቂት የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች አገራቸውን ለአንድ ዓመት ሊያገለግሉ በየጠቅላይ ግዛቱና በየአውራጃው ይላካሉ። እንዲህ አድረጌም አገልግሎት የለም!! "እሰይ የኔ ልጆች" አትልም እንዴ ኢትዮጵያችን?

ግን አላለችም !! ልትልም አይገባትም። ለምን ? እንዴት ? የጨዋ ልጅ ጥያቄ ነው ይሉናል። እንድናነሳ የሚያስፈልግ ጥያቄ ነው። ጨዋነቱ ይድረሰንና እስኪ እኒህን ጥያቄዎች ጠይቀን ብንችል መልስ እንስጣቸው።

ኋላ መጥ ሆነን አላማው በትክክል ባይገባንም እንደሌላው ብዙ ነገር ሁሉ ያለፈው የጫነብንን ሸክም ያለማማረር ብንቀበልም ወይ አገልግሎት ከመሄዳችንም በፊት ሆነ ከሄድን በኋላ ስለዓላማው በብዙ እንኳን ባይሆን በትንሹ ሳናስብበት አልቀረንም።

ስለዚህ ነበር አንዳንዶቻችን መስመር የለወጥነው። ይሻል እንደሆነ በሚል ስሜት ሳይሻል ቀረ እንጂ ለምን እንዲህ?/እንዲህ የሚለው ቃል በኋላ ይብራራል/ ሆነ ? ሃሳበ ጠባቦች ምናልባት በዳይሬክተር ክፋት ወይም በእንደራሴ አለመተባበር ያመካኙ ይሆናል።ጠለቅ ብለን ከመረመርነው ግን ወደ መሰረቱ ወደ ብሔራዊ አገልግሎት ድርጅት መሠረታዊ አቋም ይመልሰናል።

እንደ እኔ ከሆነ ብሔራዊ አገልግሎት በኢትዮጵያችን ሲቋቋም አስፈላጊነቱ ተጠንቶ ሳይሆን እንደሌላው ነገር ሁሉ /ፓርላማ፣ዩኒቨርስቲ፣ ካቢኔ፣ አምባሳደሮች/ ሌሎች ያደረጉት ነገር ቀርቶባት ኢትዮጵያችን ሆድ እንዳይብሳትና ከእህቶቿ ጋር እኩል እንድትሰለፍ ነው።ሁላችንም በዚህ መልክ የምናየው ከሆነ ደስ ይበለን ደስ ይበላችሁ ምኞታችን ፍላጐቷ ተፈጽሟል። አዎ ግን ዓይንን ቢጨፍኑት ሕሊና ያያል።ስለሆነም ያየሁትንና የታዘብኩትን ልናዘዝ።

ለባለህበት ሂድ ሊቅ **ለበረከት** ትችት ተራማጁ ቶም ፔን ሲመልስ ያለፈው ትውልድ ባለፈ ዘመን ኑሮ አልፏል ። መቃብር ሆኖ ያሁኑን ትውልድ ዕድል ሊወስን አይችልም። ያለንበት ዘመን ለኛ ላለነው ስለሆነ የራሳችንን የኑሮ ፍልስፍና እንዳንከተል የሚከለክለን ኃይል የለም። ቢኖርም እንደመስሰዋለን ብሏል። ይህ ነው ፍሬ ነገሩ ይህ ነው ሚስጥሩ።

ባለፉት ዓመታት ብሔራዊ አገልግሎት የሄዱና የተመለሱት የአገልግሎቱን ረዥም የዕረፍት ጊዜ አድርገውት ቢመለሱ እኛም የነሱን ኮቴ አስፈላጊ ሆኖ ካላገኘነው በስተቀር እንድንከተል አንገደድም። አዲስ አበባ ያለው የብሔራዊ *አገልግሎት ድርጅት ወደ ላካቸው ቦታ* ዓይናቸውን ጨፍነው እንደሄዱ መሄድ አልነበረብንም። ምናልባት ስላላወቅን ሊሆን ይችላል፣

ማሳወቅ የነሱ ፋንታ ነበር። እነሱ ቢዘነጉት ለሚመጡት የማሳወቅ ተራ የኛ ነው። ለዚህ ነው ልመነጭር የተነሳሁት።

የብሔራዊ አገልግሎት ዓላማ በየትምህርት ቤቱ ማስተማር ከሆነ ምስጋና ይድረስ የአሜሪካን መንግስት የሚበቃ የሰላም ጓዶች ልኳል።ቢያንስ ግብር ጨመር አድርጐ ከህንድ በርካሽ ይገዛል። ይህ ሊሆን ከቻለ የኛ ጉልበት የማያስፈልግ (በዚህ መስመር) የሰው ኃይል ነው እንበላ!!

በሌሎች አገሮች እንዳየነው ከሆነ (ይህም የውጭ እጅ አለበት ያሰኝ ይሆን!!) ብሔራዊ አገልግሎት ማለት እንዲህ ቀልድ ሳይሆን ከልብ የመነጨ ብሔራዊ መድህን የሆነ እውነተኛ አገልግሎት ነው። በብሔራዊ ደረጃ የመማርንና የማወቅ ፍላጐት ኖሮአቸው ዕድል ያላገኙትንና የሌሎችን (የኛን) ለማሻሻል ላባቸውን ጨምቀው ብር የሚያደርጉትን ሠራተኛውንና ገበሬውን ሕዝብ ዓይኑን እንዲገልጥ ለማድረግ የሚደረግ ከባድ ጥረት ነው።

(ለምሳሌ የሚሉ ቢኖሩ ከሩቅ ኩባ መቶ ከመቶ ሕዝቡ የተማረ ሊሆን የበቃው በተማሪዎች ብሔራዊ አገልግሎት ነው፣ ከቅርብ ታንዛኒያ) የከተማዎቹንማ ትምህርት ሚኒስቴር የሠራተኛውንና የገበሬውን ብዙ ሚሊዮን ብር እያፈሰሰ የሀገርና የውጭ አገር አስተማሪዎችን በመቅጠር አቅም ሲያንሰው የወዳጆችንን የአሜሪካንን መንግሥት የሰውና የገንዘብ ኃይል በመጠየቅም ያስተምራል።በትንሽ ብዙ ለሚያገኘው ለከተሜው ይህ መች አነሰ። የኛ መጨመርስ የምን ማብቂያ ነው፣ "የክርስቲያን ሐገር ላለው ይጨመርለታል" የሚለውን የመጽሐፍ ቃል በሥራ ለማዋል ነው መሰል።

ምሩን እንደቀልድ ማቅረብ የሚወደው ጓድ ስለብሔራዊ አገልግሎት ዓላማና የሥራ ውጤት ሲተች በግቢ አቀፍ ደረጃ (መቃብር ልበለው) ተምረን አስተምረናል፣ በከተማ አቀፍ ደረጃ የሴተኛ አዳሪዎችን ኑሮ አሻሽለናል። ለብሔራዊ አገልግሎት ድርጅት ኃላፊዎች ረዥም የእረፍት ቀናት ከወፍራም የቀን ዓበል ጋር ዳርገናል። ይህ ለሌሎች የሠራነው ነው። ለራስ ጉንም ደግሞ ብዙ ነገር ተምረናል። እኔ እንደምታውቀው ዳንስ አልችልም ነበር፣ አሁንማ የየሳምንቱ ፓርቲ ኮከብ ነኝ። ካርታ እንኳን መጫዎት የጀመርኩት እዚህ ነው። መጠጥ ቤት መሄድ አፍር ነበር። ሴት እንኳን ያወቅሁት እዚህ ነው። ትንሽ ትምህርት መች አነሰ ይለዋል እየሳቀ። እሱስ ትንሽ አይደለም፣ በብዙ ወጭ ሆነ እንጂ፣ እነዚህን ነገሮች ሁሉ በቅድሚያ ያወቁስ ምን አዲስ ትምህርት ተምረው ይሆን? በኔ በኩል ረዥም የዕረፈት ቀን ሲደመርበት ረዥም የእንቅልፍ ውጤት ሥር የሰደደ ስንፍና!! ያንን ወረቀት ለማግኘት ያኛውን ወረቀት ማን ይጽፍ ይሆን?

አንዳንድ ተማሪዎች ከኃላፊነት ለመራቅ የመስፍንን ተረት ይዘው "መቼ በወጉ ላኩንና ከዚህ የተሻለ ዓቢይ ነገር እንሠራለን" ይላሉ። ነገር ግን ማየት፣ ማጥናትና መወሰን አቅቶን

በወጉ እስከንላክ ወይም የምንሰራው እስኪነገረን የምንጠብቅ ከሆነ ለመጠበቅ ባንድፊቱን የአስተካካዩን የክርስቶስን ዳግም መምጣት መጠበቅ ይሻላል።

እርቃነ ሥጋውን የሚሄድ ሕዝብ፣ የዛፍ ፍሬ ፣ የላም ጡት ጠብቶ የሚኖር ዜጋ በዘመነ ድንጋይ ዳቦ ማረሻ የሚቆፍር (ቀብሩን)ገበሬ፣ "ሀ" የማያውቅ ሃያ ሚሊዮን ምን ልበለው

"ተነከፉ ርቆ ባዶ ቆርቆሮ" ብሏል አሉ አንድ ያውም መሪ ! ሰው ሰውነቱ አይካድም ያላት አገር እንደ "ብሔራዊ አገልግሎት" ያለውን ድርጅት እንዲህ በቀላል ወስኖ ከባድ ሥራ ሊሰርፅበት የሚችለውን ውድ ዓመት ለእንትን፣ ለስም የለሽ ከንቱ ነገር ማባከን ከስህተትም በላይ ወንጀል ነው።

የእያንዳንዱ ምሁር ጭንቅላት የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለሆነ "በጠቅላይ ኦዲተር" (ይህም ቀልድ ነው) ቁጥጥር ስር ይዋል ባንልም እንኳን የሕዝብ ሀብት ሕዝብ ይበልጥ በሚፈልገው መንገድ መዋል ስለሚገባው ለጊዜው እንዲህ ባሉ ነገሮች ላይ የህዝቡን የበላይነት የሚያውቁት የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ስለሆኑ ከፍተኛ ደረጃ ያለው ኃይል አጉል ቦታ ከማዋል እንዲድን የብሔራዊ ድርጅቱን አቋም እንደገና አጥንቶ ተገቢ እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት አለባቸው።

ይህን ድርጅት ለባለመብቱ ለኢትዮጵያ ገበሬና ሠራተኛ ሕዝብ ጥቅም እንዲውል ስናደርግ ፍሬ እየለቀሙ ለባለግብር የሚከፍለው "የሸዋ ጊሚራ" "ሻንቅላ" ግብር ከፍሎ(ከየት እንደሚያመጣው እንጃ) ተራፊውን ገንዘብ በብጣቂ ጨርቅ ቋጥሮ ከጆሮው ላይ ሰክቶ ራቁቱን የሚንዘላዘለው "የማጂው ቲርማ" (የቱሪስት ድርጅት ይህን ያውቅ ይሆን? ጥሩ የገቢ ምንጭ ነበር፤ በማስታወቂያ ቢያወጣ፣ ቱሪስትን ይስባል) ቀን አልፎ ሌት፣ ሌት አልፎ ቀን ሲመጣና ዓይኑን ሲገልጥ እጥፍ ድርብ ያስከፍለናል።

ስለዚህ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የጥናት ጓድ ተቋቁሞ የብሔራዊ አግልግሎት ተካፋዮች ያለፉትም ሆኑ ያሁኑ የሚጠበቅባቸውን ያህል ሰርተው እንደሆነ፣ ካልሰሩ (እኔ አልሰራሁም እላለሁ። ሌላ የሥራ ዓይነት ቢሰጠኝ ዓይኔን ሳላሽ እሄዳለሁ።) ሙያቸው በተገቢው ቦታ እንዲውል እንዲያደርግ አሳስባለሁ። ኮሚቴው ጥናቱን በሚጀምርበት ጊዜ ለሚደረገው ዝርዝር ምርምር የሚረዱ መረጃዎችን አዘጋጅቼ ላቀርብ በቅድሚያ ቃል እገባለሁ።

ዋለልኝ መኰንን (ታገል- ጥቅምት 1962 ዓ.ም )